የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARITGAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13[th] Year No.39
ADDIS ABABA- 23 July , 2007

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፫/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ...ገጽ ፫ሺ፮፻፴፫

CONTENTS

Proclamation No.533/2007

Broadcasting Service Proclamation.... Page 3633

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፫/፲፱፻፺፱

## ስለብሮድካስት አገልግሎት የወጣ አዋጅ

የብሮድካስት አገልግሎት ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርትና የመዝናኛ ፕሮግራም ለሕዝብ በማቅረብ ለአንድ አገር ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑ፤

የብሮድካስት አገልግሎት በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጡ ሀሣብን በነፃ የመግለጽ፣ መረጃ የማግኘት፣ የመምረጥ፣ የመመረጥና የመሳሰሉትን መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወት፤

ውስን የአገር ሀብት የሆነውን የሬዲዮ ሞገድ በአግባቡ እና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

የብሮድካስት አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሰዎችን መብትና ግዴታ በግልፅ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

እነዚህን አላማዎች ከግብ ለማድረስ በሥራ ላይ ያለውን የብሮድካስት ሕግ በተሻሻለ ሕግ መተካት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 533/2007

## A PROCLAMATION ON BROADCASTING SERVICE

**WHEREAS**, broadcasting service plays a significant role in the political, economic and social development of the country by providing information, education and entertainment programs to the public;

**WHEREAS**, broadcasting service plays a major role in exercising the basic constitutional rights such as freedom of expression, access to information and the right to elect and be elected;

**WHEREAS**, it is essential to ensure proper and fair utilization of the limited radio wave wealth of the country;

**WHEREAS**, it has been found essential to clearly define the rights and obligations of persons who undertake broadcasting service;

**WHEREAS**, to these ends, it has become necessary to revise the existing law on broadcasting services;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፫/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪ ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩/ "የሬዲዮ ሞገድ" ማለት በዓለም የቴሌኮሙኒኬሽን ማኅበር የሬዲዮ ደንብ መሠረት ለብሮድካስት አገልግሎት የተመደበ የሬዲዮ ሞገድ ነው፤

፪/ "የብሮድካስት አገልግሎት" ማለት ሕዝብን ለማስተማር፣ ለማሳወቅ ወይም ለማዝናናት የሚከናወን የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ሥርጭት አገልግሎት ነው፤

፫/ "ባለፈቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሲሆን ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ጀምሮ በሕጋዊ መንገድ የብሮድካስት አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለ ሰውንም ይጨምራል፤

፬/ "ፕሮግራም" ማለት በድምጽ ወይም በምስል ወይም በሁለቱ ተቀነባብሮ ለማሳወቅ፣ ለማስ ተማር ወይም ለማዝናናት ወይም ሁሉንም አካቶ የሚቀርብ የፕሮግራም ሥርጭት ነው፤

፭/ "ማስታወቂያ" ማለት ዕቃዎችና አገልግሎቶች እንዲታወቁና እንዲሸጡ የሚተላለፍ መልዕ ክት ነው፤

፮/ "የምርጫ ውድድር ማስታወቂያ" ማለት አንድ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ዕጩ ተወዳዳሪ እራሱንና ፍላጎቱን ለማስተዋወቅ ገንዘብ በመክፈል ወይም ለመክፈል ቃል በመግባት በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን የሚያስነግረው ማስታወቂያ ነው፤

፯/ "በስፖንሰር የሚቀርብ ፕሮግራም" ማለት ፕሮግራሙን ለማሰራጨት ገንዘብ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተከፈለበት ወይም የክፍያ ቃል የተገባበት ፕሮግራም ነው፤

፰/ "የምርጫ ወቅት" ማለት የምርጫ ውድድር በይፋ ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ ድምጽ መስጠት ከሚጀመርበት ቀን ፵፰ ሰዓት በፊት ድረስ ያለው ጊዜ ነው፤

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Broadcasting Service Proclamation No. 533/2007".

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "radio wave" means a radio wave assigned to broadcasting service in accordance with the radio regulations of the International Telecommunication Union;

2/ "broadcasting service" means a radio or television transmission program conducted to educate, inform or entertain the public;

3/ "licensee" means a person licensed in accordance with this Proclamation, and includes a person lawfully engaged in rendering broadcasting service before the enactment of this Proclamation;

4/ "program" means voice or visual or audiovisual arrangement transmitted to inform, educate or entertain the public, or an all inclusive transmission program;

5/ "Advertisement" means a message transmitted to publicize and promote sales of goods and services;

6/ "election campaign advertisement" means a radio or television message conveyed by a political organization or candidate to publicize about himself and his aspirations by paying or promising to pay for the announcement;

7/ "sponsored program" means a program the transmission cost of which is paid directly or indirectly or the payment of which is promised;

8/ "election period" means the period beginning from the official opening day of a campaign until 48 hours before the starting of voting day;

፱/ "የመንግሥት ብሮድካስት አገልግሎት" ማለት ሕዝብን ለማስተማር፣ ለማሣወቅና ለማዝናናት በአገር አቀፍ ወይም በክልል የሚቋቋም ተጠሪነቱም ለፌደራል የሕዝብ ተወካዮች ወይም ለክልል ምክር ቤቶች የሆነ በሙሉ ወይም በከፊል የመንግሥት በጀት የተመደበለት የሬዲዮ ወይም የቴሌቭዥን አገልግሎት ነው፤

፲/ "የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት" ማለት ትርፍን መሠረት ያደረገ፣ ሕዝብን ለማስተማር፣ ለማሣወቅና ለማዝናናት ሕጋዊ ሰውነት ባለው አካል የተቋቋመ የሬዲዮ ወይም የቴሌቭዥን አገልግሎት ነው፤

፲፩/ "የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት" ማለት በአንድ በተወሰነ አካባቢ በሚኖሩ ወይም የጋራ ፍላጎት በሚያገናኛቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች በፍላጎት የተቋቋመና በማኅበረሰቡ የሚተዳደር እና የሚመራ ለትርፍ ያልቆመ የሬዲዮ ወይም የቴሌቭዥን አገልግሎት ነው፤

፲፪/ "የፖለቲካ ድርጅት" ማለት በሕጋዊ መንገድ የፖለቲካ ፕሮግራሙን የሚያራምድ ቡድን ነው፤

፲፫/ "አመልካች" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱(፫) የተጠቀሰውን የማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ለባለሥልጣኑ ያቀረበ ሰው ነው፤

፲፬/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፭/ "አገር አቀፍ ስርጭት" ማለት ከአንድ ክልል በላይ የሚሸፍን የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

፲፮/ "ክልላዊ ስርጭት" ማለት ስርጭቱ በአንድ ክልል ብቻ የተወሰነ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

፲፯/ "አካባቢያዊ ስርጭት" ማለት ስርጭቱ በአንድ ወረዳ ወይም ማዘጋጃ ቤት ብቻ የተወሰነ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

፲፰/ "አገራዊ ፕሮግራም" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ በኢትዮጵያዊያን የተዘጋጀ ፕሮግራም ነው፤

፲፱/ "ሚኒስቴር እና ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የማስታወቂያ ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤

9/ "public broadcasting service" means a radio or television transmission service established, for the purpose of educating, informing and entertaining the public, in the federal or a regional state to which government budget is allocated in full or in part and is accountable to the Federal House of Peoples Representatives or to Regional Councils;

10/ "commercial broadcasting service" means a radio or television transmission service established for profit by a legal entity with the purpose of informing, educating or entertaining the public;

11/ "community broadcasting service" means a non-profit radio or television transmission service established by the will and interest of a community and Administered and run by the community living in a specific area or who possess a common interest;

12/ "political organization" means a grouping legally promoting its political program;

13/ "applicant" means a person who fills and submits an application form to the Authority as indicated under Article 19(3) of this Proclamation;

14/ "regional state" means any of the regional states specified under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

15/ "national transmission" means a broadcasting service whose transmission covers more than one regional state;

16/ "regional transmission" means a broadcasting service whose transmission is limited to one regional state only;

17/ "local transmission" means a broadcasting service whose transmission is limited to one wereda or one municipality only;

18/ "national program" means a program prepared in Ethiopia by Ethiopians;

19/ "Ministry" and "Minister" means the Ministry and Minister of Information, respectively;

፳/ "ኢንስፔክተር" ማለት ባለፈቃዶች ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን አክብረው መሥራታቸውን የሚቆጣጠር በባለሥልጣኑ የሚመደብ ሠራተኛ ነው፤

፳፩/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

## ፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋሙ በመንግ-ሥት፣ በንግድ እና በማኅበረሰብ የብሮድካስት አገልግሎቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል::

## ክፍል ሁለት
## የብሮድካስት ባለሥልጣን

## ፬. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ የብሮድካስት ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

፪/ ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል::

## ፭. ዋና መሥሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በአገሪቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል::

## ፮. ዓላማ

የባለሥልጣኑ ዓላማ ለፖለቲካዊ፣ ለማኅበራዊና ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያደርግ፣ ጥራቱ የተጠበቀ፣ ቀልጣፋና አስተማማኝ የብሮድካስት አገልግሎት እንዲስፋፋ ማድረግና መቆጣጠር ይሆናል::

## ፯. ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ለአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ ሊያበረክት በሚችል መልኩ መካሄዱን ያረጋግጣል፤

20/ "inspector" means a person assigned by the Authority to supervise the proper observance, by licensees, of the provisions of this Proclamation and regulations and directives issued hereunder;

21/ "person" means a physical or juridical person.

## 3. Scope of Application

This Proclamation shall be applicable to government, commercial and community broadcasting services established within Ethiopia.

## PART TWO
## Broadcasting Authority

## 4. Establishment

1/ The Ethiopian Broadcasting Authority (hereinafter "the Authority") is hereby established as an autonomous federal agency having its own legal personality.

2/ The Authority shall be accountable to the Ministry.

## 5. Head Office

The Authority shall have its head office in Addis Ababa and may establish branch offices elsewhere as may be necessary.

## 6. Objectives

The objectives of the Authority shall be to ensure the expansion of a high standard, prompt and reliable broadcasting service that can contribute to political, social and economic development and to regulate same.

## 7. Powers and Duties

The Authority shall have the powers and duties to:

1/ ensure that the broadcasting service is conducted in such a manner that contributes to the proper social, economic, political and cultural development of the country;

፪/ ለብሮድካስት አገልግሎቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

፫/ የብሮድካስት ጣቢያ የሚቋቋምበትን ሥፍራና የሽፋን ክልል ከሌሎች የሬዲዮ ኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ጋር አለመጋጨቱን አረጋግጦ ይወስናል፤

፬/ ለብሮድካስት አገልግሎት የሚውሉትን መሣሪያዎች ዓይነትና ደረጃ እንዲሁም የማሠራጫ መሣሪያውን ጉልበት ይወስናል፤

፭/ ሕገወጥ ሥርጭትን በሚመለከት ቁጥጥር ያደርጋል፤

፮/ ለብሮድካስት አገልግሎት በሚመለከተው አካል የተመደበውን የሬዲዮ ሞገድ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ይፈቅዳል፣ ይቆጣጠራል፣ ያከራያል፤

፯/ ስለብሮድካስት አገልግሎት ዕድገትና መሻሻል ጥናት ያደርጋል፣ አገልግሎቱን የሚመለከቱ መረጃዎችን አጠናቅሮ ይይዛል፤

፰/ ለተለያዩ የብሮድካስት አገልግሎቶች የቴክኒክ ደረጃዎች ያወጣል፤

፱/ የብሮድካስት መሣሪያዎችን ደረጃ ያወጣል፤ ለመሣሪያዎቹ አስመጪዎች የማረጋገጫ ሰርትፊኬት ይሰጣል፣ አሰራራቸውንም ይቆጣጠራል፤

፲/ በብሮድካስት አገልግሎት በሚነሱ ቅሬታዎች ላይ ውሣኔ ይሰጣል፤

፲፩/ አግባብ ያላቸው ሕጎችና የመንግሥት መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው የብሮድካስት አገልግሎትን በሚመለከት መንግሥትን በመወከል በዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ይሳተፋል፤ የብሮድካስት አገልግሎትን በሚመለከት አገሪቱ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አፈጻጸም ይከታተላል፤

፲፪/ የብሮድካስት አገልግሎት የፈቃድ ክፍያዎችን ተመን ያወጣል፣ ይሰበስባል፤

፲፫/ በሚመለከተው አካል ለሚመደበው የሬዲዮ ሞገድ ተገቢውን ክፍያ ይፈጽማል፤

፲፬/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲፭/ ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ያከናውናል::

2/ issue, suspend and cancel broadcasting service licenses;

3/ determine the site and coverage area of a broadcasting station to avoid an overlap with any radio communication;

4/ determine the type and standard of equipments to be used for a broadcasting service as well as the capacity of the transmitter;

5/ control illegal transmissions;

6/ plan, permit and control the use of the radio wave allocated for broadcasting service by the concerned organ and lease same;

7/ conduct study with regard to the development and improvement of the broadcasting services; compile and maintain information related to the services;

8/ prescribe technical standards for different categories of broadcasting services;

9/ prescribe standards for broadcasting equipments; issue certificates of compliance to importers of the instruments and supervise their operations;

10/ decide on complaints arising in relation to broadcasting services;

11/ without prejudice to the relevant laws and Government directives participate, on behalf of the Government, in international meetings on matters related to broadcasting services; follow up the implementation of international agreements on broadcasting services to which the country is a party;

12/ fix and collect license fees for broadcasting services;

13/ pay the appropriate fee for the radio wave allocated by the concerned organ;

14/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

15/ perform other acts as are required for the implementation of its objectives.

## ፰. የባለሥልጣኑ አቋም

ባለሥልጣኑ፣

፩/ ቦርድ፣
፪/ ዋና ዳይሬክተር፣
፫/ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ እና
፬/ አስፈላጊ ሠራተኞች፣
ይኖሩታል::

## ፱. ስለቦርድ አባላት

፩/ ቦርዱ በመንግሥት የሚወሰን ቁጥር ያላቸው አባላት ይኖሩታል::

፪/ የቦርዱ አባላት ከተለያዩ ተቋማትና የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ሆነው በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግስት የሚመደቡ ይሆናሉ::

፫/ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ አባል እና ፀሀፊ ይሆናል::

፬/ የቦርዱ ተጠሪነት ለማስታወቂያ ሚኒስቴር ይሆናል።

## ፲. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩/ የዚህን አዋጅ አፈጻጸምና የባለሥልጣኑን ሥራዎች በበላይነት ይቆጣጠራል፤

፪/ የባለሥልጣኑን አመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት እንዲሁም የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ይገመግማል፤

፫/ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚወጡ መመሪያዎችን መርምሮ እንዲፀድቁ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤

፬/ አመልካቾችና ባለፈቃዶች የሚያቀርቧቸውን አቤቱታዎች መርምሮ ይወስናል፤ ባለፈቃዶችን አስመልክቶ ከሕዝቡ በቀረቡ ቅሬታዎች በተሰጡ ውሣኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ይወስናል፤

፭/ የዚህን አዋጅ አፋጻጸም በሚመለከት በሚቀርቡለት የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ እንደአግባቡ ይወስናል::

## 8. Organization of the Authority

The Authority shall have:

1/ a Board;
2/ a Director General;
3/ a Deputy Director General; and
4/ the necessary staff.

## 9. Members of the Board

1/ The number of members of the board shall be determined by the Government.

2/ Members of the Board shall be drawn from different institutions and parts of the society and shall be appointed by the Government on the recommendation of the Minister.

3/ The Director General of the Authority shall be a member and secretary of the Board.

4/ The Board shall be accountable to the Ministry.

## 10. Powers and Duties of the Board

The Board shall have the powers and duties to:

1/ oversee the implementation of this Proclamation and the activities of the Authority;

2/ review the annual work programs and budgets as well as the activity reports of the Authority;

3/ review and submit to the Ministry, for its approval, directives to be issued for the implementation of this Proclamation;

4/ examine and decide on complaints brought by applicants and licensees; examine and decide on appeals on decisions given against broadcasters on the basis of public complaints;

5/ deliberate and, as may be appropriate, decide on policy matters pertaining to the implementation of this Proclamation.

## ፲፩. የቦርዱ ስብሰባ

፩/ ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል::

፪/ በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል::

፫/ የቦርዱ ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል::

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል::

## ፲፪. ስለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር

፩/ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት ይሾማል::

፪/ ዋናው ዳይሬክተር የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል::

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ዳይሬክተር፣

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ አግባብ ባለው አካል ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው የሥራ ፕሮግራምና በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

## 11. Meetings of the Board

1/ The Board shall meet once every month; provided, however, that it may convene at any time when called by the chairperson.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members are present at a meeting of the Board.

3/ Decisions of the Board shall be passed by majority votes; in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the board may adopt its own rules of procedure.

## 12. Director General of the Authority

1/ The Director General of the Authority shall be appointed by the Government upon recommendation by the Minister.

2/ The Director General shall be the chief executive of the Authority and, subject to the general directives of the Board, shall direct and administer the activities of the Authority.

3/ Without limiting the generality of the provisions of sub-article (2) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Authority stated under Article 7 of this Proclamation;

b) employ and administer employees of the Authority in accordance with directives to be approved by the Government following the basic principles of the federal civil service laws;

c) prepare and submit to the Board the work program and budget of the Authority, and implement same when approved by the appropriate organ;

d) effect expenditure in accordance with the work program and budget of the Authority;

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ረ) የባለሥልጣኑን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

ሰ) በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል::

፬/ ዋናው ዳይሬክተር ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሊያስተላልፍ ይችላል::

## ፲፫. ስለባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር

፩/ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት ይሾማል::

፪ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ከዋናው ዳይሬክተር በሚሰጠው መመሪያ መሠረት፣

ሀ) በሥሩ የተመደበለትን የሥራ ዘርፍ ይመራል፣ ያስተባብራል፤

ለ) በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል::

## ፲፬. በ ጀ ት

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግስት የሚመደብ ይሆናል::

## ፲፭. ስለሂሳብ መዛግብት

፩/ ባለስልጣኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል::

፪/ የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየአመቱ ይመረመራሉ::

## ክፍል ሦስት
## የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ

## ፲፮. የብሮድካስት አገልግሎት ዓይነቶች

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ዓይነቶች የመንግሥት፣ የንግድና የማኅበረሰብ ይሆናሉ::

e) represent the Authority in all its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Board the activity and financial reports of the Authority;

g) perform such other duties as may be assigned to him by the Board.

4/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officials and employees of the Authority to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Authority.

## 13. Deputy Director General of the Authority

1/ The Deputy Director General shall be appointed by the Government upon recommendation by the Minister.

2/ The Deputy Director General shall, subject to the directives of the Director General:

a) direct and co-ordinate units placed under his supervision; and

b) perform other activities assigned to him by the Director General.

## 14. Budget

The budget of the Authority shall be allocated to it by the Government.

## 15. Books of Accounts

1/ The Authority shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The accounts and financial documents of the Authority shall be audited annually by the Auditor General or an auditor assigned by him.

## PART THREE
## BROADCASTING SERVICE LICENSES

## 16. Categories of Broadcasting Services

1/ Categories of broadcasting services shall be public, commercial and community broadcasting services.

፪/ ማንኛውም የመንግስት የብሮድካስት አገልግሎት፣

ሀ) የመንግሥት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጅዎችን እንዲሁም የልማት፣ የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር እንቅስቃሴዎችን በማቅረብ የሕዝቡን ተሣትፎ ያዳብራል፤

ለ) ሕዝቡን የሚያሳውቁ፣ የሚያስተምሩና የሚያዝናኑ ፕሮግራሞችን ያቀርባል፤

ሐ) በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የሕዝቦችን አንድነት የሚያንፀባርቁ ፕሮግራሞችን ያቀርባል፤

መ) የሕዝቡን ባህልና ጥበባዊ እሴቶች ያስተዋውቃል፣ ያጎለብታል፤

ሠ) በአገሪቱ ሕገ መንግሥትና የምርጫ ሕግ መሠረት የሚንቀሣቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችን በፍትሃዊነት ያገለግላል።

፫/ ማንኛውም የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ለትርፍ ዓላማ የተቋቋመ ቢሆንም፣

ሀ) ፈቃድ በወሰደበት አካባቢ የሚገኘውን ኅብረተሰብ በእኩልነት ያስተናግዳል፤

ለ) ፈቃድ ለወሰደበት አካባቢ አገልግሎቱን ያደርሳል፤

ሐ) በፕሮግራሙ ውስጥ አካባቢያዊና አገራዊ ዜናዎችን ያካትታል።

መ) በባለስልጣኑ የተሰጠውን ፈቃድ እንደአግባብነቱ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ለክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ በማቅረብ ማስመዝገብ አለበት።

፬/ ማንኛውም የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት፣

ሀ) የማኅበረሰቡን የልማት፣ የትምህርትና የመልካም አስተዳደር ፍላጎቶች መሠረት አድርጎ ይሰራል፤

ለ) የማኅበረሰቡን ቋንቋ፣ ባህልና ጥበባዊ እሴቶች ያስተዋውቃል፣ ያጎለብታል፤

ሐ) በፕሮግራም ዝግጅት የማኅበረሰቡን አባላት ያሳትፋል፤

2/ Any public broadcasting service shall:

a) enhance the participation of the public through the presentation of government policies and strategies as well as activities related to development, democracy and good governance;

b) present programs which inform, educate and entertain the public;

c) present programs which reflect unity of peoples based on equality;

d) promote and enhance the cultures and artistic values of the public;

e) serve political parties operating in accordance with the Constitution and the electoral laws of the country on the basis of fair and just treatment.

3/ Notwithstanding its profit-making objective, any commercial broadcasting service shall:

a) provide equal treatment to any community in its license area;

b) transmission. of its programs shall cover the whole area of its license;

c) include regional and national news in its programs.

d) Submit to register the license given by the authority to the Ministry of Trade and Industry or to the Regional Trade and Industry Bureau.

4/ Any community broadcasting service shall:

a) carry out its activities based on the needs of the community regarding development, education and good governance;

b) promote and develop the language, culture and artistic value of the community;

c) allow the participation of the members of the community in the preparation of its programs;

መ) ሌሎች የማሠራጫ አገልግሎቶች ሊያሠራጩ ያልቻሉትን የማኅበረሰቡን የጋራ ጉዳዮች የሚመለከቱ ፕሮግራሞች ያሰራጫል፤

ሠ) ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ ገቢዎችን ለማሰራጫ ጣቢያው አገልግሎት ያውላል፤

ረ) ለማኅበረሰቡ ጠቀሜታ ያላቸውንና ማኅበረሰቡን መሠረት ያደረጉ አስፈላጊ መረጃዎችንና የመዝናኛ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት የማኅበረሰቡን የመረጃ ባህልና እውቀት ያዳብራል።

፲፯. የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አይነቶች

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፤

ሀ/ ከምድር ወደ አየር ነፃ የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት፣

ለ/ ከምድር ወደ አየር ነፃ የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት፣

ሐ/ በሳተላይት አማካይነት የሚሰራጭ የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት፣

መ/ በሳተላይት አማካይነት የሚሠራጭ የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት፣

ሠ/ በሳተላይት አማካይነት በክፍያ ለደንበኞች የማድረስ ብሮድካስት አገልግሎት፣

ረ/ የውጪ ፕሮግራሞችን በመቀበል ለደንበ ኞች በክፍያ የማድረስ ብሮድካስት አገልግ ሎት፣

ሰ/ በኬብል አማካይነት የቴሌቪዥን ፕሮ ግራም ለክፍያ ለደንበኞች የማድረስ ብሮድካስት አገልግሎት፤

ሸ/ ሌሎች ባለሥልጣኑ የሚወስናቸው የፈቃድ ዓይነቶች።

፲፰. የፈቃድ አስፈላጊነት

፩/ ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድ ሳይሰጠው በብሮድካስት አገልግሎት ሥራ ላይ መሠማራት አይችልም።

፪/ አንድ ባለፈቃድ በአንድ ፈቃድ ከአንድ ማሰራጫ ጣቢያ በላይ ማቋቋም አይችልም።

d) transmit programs on issues involving the common interests of the community that could not get coverage by other broadcasting services;

e) utilize the income derived from different sources for the operation of the broadcasting station;

f) provide community centered informative and entertaining programs to promote the information culture and knowledge of the community.

**17. Categories of Broadcasting Service Licenses**

1. Categories of broadcasting service licenses shall be the following:

a/ terrestrial to air free radio broadcasting service;

b/ terrestrial to air freetelevision broadcasting service;

c/ satellite radio broadcasting service;

d/ satellite television broadcasting service;

e/ Satellite broadcasing service provided to customers for fee;

f/ receiving and broadcasting forergn programs to customers for fee;

g/ cable television broadcasting service provided to customers for fee;

h/ other broadcasting services to be prescribed by the Authority.

**18. Requirement of License**

1/ No person may undertake broadcasting service without obtaining a broadcasting service license from the Authority.

2/ A broadcasting service licensee may not operate more than one broadcasting station with one license.

## ፲፱. አመልካቾችን ስለመጋበዝ

፩/ ባለሥልጣኑ አመልካቾችን ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በሌሎች መገናኛ ብዙኃን በሚገለጽ ማስታወቂያ ይጋብዛል።

፪/ ማስታወቂያው ለመፍቀድ የታሰበውን የብሮድካስት አገልግሎት አይነት፣ አገልግሎቱ የሚሸፍነውን አካባቢ፣ ዝግጁ የሆነውን የሬዲዮ ሞገድ፣ የማመልከቻ ማቅረቢያውን ጊዜና ቦታ፣ የፈቃዱን ክፍያና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን መያዝ አለበት።

፫/ በብሮድካስት አገልግሎት ሥራ ላይ ለመሠማራት የሚፈልግ ሰው በዚህ አንቀጽ መሠረት በሚወጣው ማስታወቂያ በሚጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ አለበት።

፬/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩)-(፫) የተደነገገው ቢኖርም የመንግሥት እና የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት አመልካች በማናቸውም ጊዜ ለባለሥልጣኑ የፈቃድ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል።

## ፳ ተቀባይነት ስለሌለው ማመልከቻ

ማንኛውም ፈቃድ እንዲሰጠው ማመልከቻ ያቀረበ ሰው፣

፩/ የፋይናንስ አቅሙንና ምንጩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሕጋዊ ማስረጃ ካላቀረበ፣

፪/ ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ካላቀረበ፣ ወይም

፫/ በአንቀጽ ፳፫ መሠረት ፈቃድ የማይሰጠው አካል ከሆነ፣

በዝርዝር ማጣራት ሳያስፈልግ ማመልከቻው ውድቅ ይሆናል።

## ፳፩. የፈቃድ መስፈርት

፩/ ባለሥልጣኑ የአመልካቾችን ብቃት ለመመዘን የሚያስችለው ዝርዝር መስፈርት ያወጣል።

፪/ በባለሥልጣኑ የሚዘጋጀው መስፈርት የሚከተሉትን ያካተተ ይሆናል፤

ሀ) አገልግሎቱን ለመስጠት የአመልካቹ የፋይናንስ አቅም ተአማኒነትና ብቃት፤

ለ) በአመልካቹ ፕሮጀክት የተዘረዘሩ መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች አገልግሎቱን ለመስጠት ያላቸው ብቃት፤

## 19. Invitation to Applicants

1/ The Authority shall invite applicants by a notice published in a newspaper having a wide circulation or communicated by other mass media.

2/ The notice shall disclose the category of broadcasting service for which the license is intended to be issued, the license area, the radio wave available, time and place of submission of the application, the license fee and other necessary information.

3/ A person who intends to obtain a license for broadcasting service shall fill and submit the application form prepared by the Authority within the time specified in the notice issued in accordance with this Article.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-articles (1)-(3) of this Article, an applicant for a public broadcasting and community broadcasting service license may apply at any time to the Authority.

## 20. Unacceptable Application

Any application may be rejected, without going into detail screening, if the applicant:

1/ fails to produce legal evidence to ascertain its financial capacity and source of financing;

2/ fails to produce detail project proposal; or

3/ is a body that may not be entitled to a license as provided for in Article 23 of this Proclamation.

## 21. Criteria for Issuance of License

1/ The Authority shall set criteria that enable it to evaluate the capability of applicants.

2/ The criteria to be set by the Authority shall include the following:

a) the reliability and sufficiency of the applicant's financial sources to run the service;

b) the capability of equipments and technologies, listed in the applicant's project proposal, to render the service;

ሐ) አመልካቹ አገልግሎቱን ለመስጠት ያለው ድርጅታዊ ብቃት፣ እውቀትና የሥራ ልምድ፤

መ) በአመልካቹ የቀረበው የፕሮግራም ይዘትና በፕሮግራሙ የተካተቱ ማኅበራዊ ፍላጎቶች፤

ሠ) ለአገልግሎቱ የተመደበው የስርጭት ጊዜ::

## ፳፪. የውሳኔ አሰጣጥ

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱(፫) መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ በአንቀጽ ፳ እና ፳፩ መሠረት ከመረመረ በኋላ ውሳኔ ይሰጣል::

፪/ ባለሥልጣኑ ፈቃድ እንዳይሰጥ ሲወስን፣ ፈቃዱ የማይሰጥበትን ምክንያት ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት::

፫/ ፈቃድ የተከለከለ አመልካች ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ፲፬ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል:: ቦርዱም አቤቱታው በደረሰው በ፳ ቀናት ውስጥ ውሣኔ መስጠት አለበት::

፬/ የፈቃድ ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ አመልካች ፈቃዱ በሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ስምምነት በመፈረምና ተገቢውን የፈቃድ ክፍያ በመፈጸም የፈቃድ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል::

## ፳፫. ፈቃድ ስለማይሰጣቸው አካላት

የሚከተሉት አካላት የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አይሰጣቸውም፤

፩/ ለግለሰብ እና በሕግ የሰውነት መብት ያልተሰጠው አካል፤

፪/ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎችን በተመለከተ በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ) ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተቋቋመ፣ ወይም

ለ) በካፒታሉ ወይም በአመራሩ የውጭ አገር ዜጎች ድርሻ ያለበት፣ ድርጅት፤

፫/ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅት ባለአክሲዮን የሆነበት ወይም የፖለቲካ ድርጅት የበላይ አመራር አባል ባለአክሲዮን ወይም በማንኛውም ደረጃ የአመራር አባል የሆነበት ድርጅት፤

c) the applicant's organizational capacity, knowledge and experience to render the service;

d) the contents of the program submitted by the applicant and social needs covered by the program;

e) the transmission time allocated for the service.

## 22. Decision Making

1/ The Authority shall, upon examining in accordance with Articles 20 and 21 of this Proclamation, decide on the application submitted to it under Article 19(3) of this Proclamation.

2/ Where the Authority decides not to issue a license, it shall communicate to the applicant the reasons thereof.

3/ Any applicant who is denied a license may appeal to the Board within 14 days from the date of the decision. The Board shall give its decision within 20 days from receipt of the appeal.

4/ An applicant whose application has been accepted shall be issued with a certificate of license upon signing a license agreement prepared by the Authority to provide for the terms and condition of the license and upon payment of the required license fee.

## 23. Bodies not to be issued with Licenses

The following bodies may not be issued with broadcasting service licenses:

1/ a body that is not conferred with a legal personality;

2/ without prejudice to the provisions of other laws regarding foreign nationals of Ethiopian origin, an organization:

a) not incorporated in Ethiopia; or

b) in which its capital or its management control is held by foreign nationals;

3/ an organization of a political organization or of which a political organization is a shareholder or a member of a political organization's supreme leadership is a shareholder or member of its management at any level;

፬/ የሐይማኖት ድርጅት፤

፭/ የድርጅቱ ባለቤት ወይም ከድርጅቱ ባለቤቶች ወይም ከአመራር አባላቱ ውስጥ በከባድ ወንጀል ተከሶ የተፈረደበት ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ከሲቪል ወይም ከፖለቲካ መብቶቹ የታገደ ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሕግ ችሎታውን ያጣ ሰው ከሆነ፤

፮/ የካፒታሉ ፶ በመቶ በላይ የሚሆነው የህትመት ፕሬስ ወይም የዜና አገልግሎት ሥራ በሚሠራ ድርጅት ወይም በእንደዚሁ ዓይነት ድርጅት ካፒታል ውስጥ ከ፳ በመቶ በላይ ድርሻ ባለው ሰው የተያዘ ድርጅት

፯/ የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ወይም ከአንድ በላይ የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ያለው ሆኖ ለቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ሌላ ፈቃድ የሚጠይቅ ድርጅት፤

፰/ በተመሳሳይ የፈቃድ ክልል የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ያለው ወይም በተለያዩ የፈቃድ ክልሎች ሁለት የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ያለው ሆኖ ለሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ሌላ ፈቃድ የሚጠይቅ ድርጅት።

## ፳፬. የብሮድካስት ፈቃድ ዘመን

የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃዶች ጸንተው የሚቆዩበት ጊዜ እንደሚከተለው ይሆናል፤

፩/ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሠራጭ ሲሆን ለሬዲዮ ፰ ዓመት፣ ለቴሌቪዥን ፲ ዓመት፤

፪/ የሥርጭት ሽፋኑ በክልል ደረጃ የተወሰነ ሲሆን ለሬዲዮ ፲ ዓመት ለቴሌቪዥን ፲፪ ዓመት፤

፫/ የሥርጭት ሽፋኑ በአካባቢ ደረጃ የተወሰነ ሲሆን ለሬዲዮ ፲፪ ዓመት፣ ለቴሌቪዥን ፲፬ ዓመት፤

፬/ የሥርጭት ሽፋኑ በድሬዳዋ የተወሰነ ከሆነ ለሬዲዮ ፲ ዓመት፣ ለቴሌቪዥን ፲፪ ዓመት፤

፭/ የሥርጭት ሽፋኑ በአዲስ አበባና አካባቢዋ የተወሰነ ከሆነ ለሬዲዮ ፮ ዓመት፣ ለቴሌቪዥን ፰ ዓመት፤

፮/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ከሆነ ፭ ዓመት፤

፯/ የአጭር ጊዜ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ከሆነ ከ፩ ዓመት ያልበለጠ።

4/ a religious organization;

5/ an organization of which its owner or any of its owners or a member of its management is convicted of a serious crime or, by decision of a court, is deprived of exercising his civil or political rights or has fully or partially lost his legal capacity;

6/ an organization of which more than 50% of its capital is held by another organization which carries on the business of printed press or news agency or a person that owns more than 20% of the capital of such organization;

7/ an organization applying for a television broadcasting service license while already having a license for television broadcasting service or more than one license for radio broadcasting service;

8/ an organization applying for a radio broadcasting service license while having a license for radio broadcasting service in the same license area or two licenses in different license areas.

## 24. Validity Period of Broadcasting Service Licenses

The validity period of broadcasting service licenses shall be as follows:

1/ where the transmission is at the national level, 8 years for radio, 10 years for television;

2/ where the transmission is limited to a regional state, 10 years for radio, 12 years for television;

3/ where the transmission is limited to local level, 12 years for radio, 14 years for television;

4/ where the transmission is limited to Dire Dawa, 10 years for radio, 12 years for television;

5/ where the transmission is limited to Addis Ababa and its surroundings, 6 years for radio and 8 years for television;

6/ for community broadcasting service 5 years;

7/ for short-term community broadcasting service not more than 1 year.

## ፳፭. ፈቃድ ስለማደስ

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የፈቃድ ጊዜ ገደቡ ሳያልቅ ከ፩ አመት ባልበለጠና ከ፮ ወራት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ባለሥልጣኑ ያዘጋጀውን የፈቃድ ማደሻ ቅጽ ሞልቶ የዕድሳት ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ከማደሱ በፊት የሬዲዮ ሞገዱ ለሌላ ተግባር አለመፈለጉን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ ባለፈቃዱ በፈቃድ ዘመኑ የሰጠው አገልግሎት በተገልጋዩ ኅብረተሰብ ተቀባይነትን ያገኘና የተደጋጋሚ ቅሬታዎች ሪከርድ የሌለበት መሆኑን ባለሥልጣኑ ማረጋገጥ አለበት፡፡

፬/ የታደሰ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ በባለሥልጣኑ ይወሰናል፡፡

## ፳፮. የማስፋፊያ ፈቃድ

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ተጨማሪ ስርጭትን ለማካሄድ፣ የጣቢያውን አቅም ለማሳደግ ወይም የቴክኖሎጂ ለውጥ ለማድረግና የማሠራጫ መሳሪያውን አቅም ለማሳደግ ከፈለገ ከባለሥልጣኑ የማስፋፊያ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

፪/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ አገልግሎት ከሚሰጥበት አካባቢ ውጭ ሌሎች አካባቢዎችን ለማዳረስ አዲስ የሬዲዮ ሞገድ ሲጠይቅ፣ ባለሥልጣኑ የማስፋፊያ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት፣

ሀ) ፈቃድ የተጠየቀበት ተጨማሪ የሬዲዮ ሞገድ በሌላ የብሮድካስት አገልግሎት አለመያዙን፣ እና

ለ) ፈቃድ የተጠየቀበትን አካባቢ የሕብረተሰብ ፍላጎት፣
ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ቀደም ብሎ ፈቃድ በወሰደበት የሬዲዮ ሞገድ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ፈቃድ ሲጠይቅ፣ የብሮድካስት አገልግሎቱን ለማስፋፋት የቀረቡት መሣሪያዎች ከታቀደው የአገልግሎት ማስፋፊያ ዕቅድ ጋር መጣጣማቸውን ባለሥልጣኑ ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ፳፯. የፈቃድና አመታዊ ክፍያ

፩/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ባለሥልጣኑ በየጊዜው እያጠና በሚወስነው መሠረት የፈቃድ ክፍያ፣ ዓመታዊ ክፍያና የፈቃድ ማደሻ ክፍያ መክፈል አለበት፡፡

## 25. Renewal of License

1/ The broadcasting service licensee shall fill and submit the license renewal form prepared by the Authority not earlier than 1 year and not later than 6 months before the expiry of the validity period of the license.

2/ Before renewing the license, the Authority shall ascertain that the radio wave is not required for another purpose.

3/ The Authority shall ascertain that the service rendered by the licensee during the validity period of license was acceptable to the community and it had no records of repeated complaints brought against it.

4/ The validity period of a renewed broadcasting service license shall be determined by the Authority.

## 26. Expansion License

1/ Any broadcasting service licensee shall obtain an expansion license from the Authority when it intends to provide additional broadcasting service, upgrade the capacity of the station or to make technological changes and upgrade the capacity of the transmitter.

2/ When a broadcasting service licensee requests a new radio wave to cover other areas outside of its license area, the Authority shall, before granting the expansion license, ascertain:

a) that the requested additional wave is not held by another broadcasting service; and

b) the need of the community of the area which the license is requested.

3/ When a broadcasting service licensee requests a technological expansion license for the radio wave licensed earlier, the Authority shall ascertain that the equipments proposed are compatible with the expansion plan of the service.

## 27. License and Annual Fee

1/ Any broadcasting service licensee shall pay license fee, annual fee and license renewal fee, as reviewed and determined from time to time by the Authority.

፪/ አመታዊ ክፍያው የመንግሥት የበጀት ዓመት በተጠናቀቀ በ፷ ቀናት ውስጥ ካልተከፈለ ለዘገየበት ለያንዳንዱ ወር ፭ በመቶ መቀጫ እየታከለበት ይከፈላል። ሆኖም የመቀጫው ጠቅላላ ድምር ከዋናው ክፍያ ፶ በመቶ ሊበልጥ አይችልም።

## ፳፰. ፈቃድን ስለማገድ

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከጣሰ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ሊያግደው ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረግ እገዳ በጽሑፍ ሆኖ እገዳው የተደረገበት ምክንያትና ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን ተገልጾ ለባለፈቃዱ እንዲደርሰው መደረግ አለበት።

፫/ በተጣለበት እገዳ ቅር የተሰኘ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የእግዱ ትዕዛዝ በደረሰው በ፲፬ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል። ቦርዱ አቤቱታው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ውሣኔ መስጠት አለበት።

## ፳፱. የብሮድካስት ፈቃድን ስለመሠረዝ

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ በባለሥልጣኑ ሊሠረዝ ይችላል፤

ሀ) ባለፈቃዱ ፈቃድ ካወጣበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሥርጭቱን ያልጀመረ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ለ) ባለፈቃዱ ፈቃዱን ያገኘው በተጭበረበረ መንገድ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ) የሥርጭት ጣቢያው ያለበቂ ምክንያት ሥርጭቱን ከአንድ ወር በላይ ሲያቋርጥ፤

መ) ጣቢያው በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲዘጋ ሲወሰን፤

ሠ) ባለፈቃዱ በራሱ አነሳሽነት ሥራውን ሲያቆም፤

ረ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴(፬) የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተጥሰው ሲገኙ፤

ሰ) ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፯ የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣ እንደሆነ።

2/ Where the broadcasting service annual fee is not paid within 60 days after the end of the Government fiscal year, a penalty of 5% shall be added for each month of delay; provided, however, that the total amount of penalty shall not exceed 50% of the license fee.

## 28. Suspension of License

1/ Without prejudice to Article 29 of this Proclamation, the Authority may suspend a broadcasting service license where the licensee violates the provisions of this Proclamation.

2/ The decision of suspension made in accordance with sub-article (1) of this Article shall be served to the licensee stating, in writing, the reasons thereto and the effective date of the suspension.

3/ The licensee may, where it is aggrieved by the suspension, submit its grievance to the Board within 14 days from the date of receipt of the suspension order. The Board shall give its decision within 30 days from the date of receipt of the grievance.

## 29. Revocation of License

1/ A broadcasting service license may be revoked by the Authority on any one of the following grounds:

a) where it is confirmed that the licensee has failed to commence transmission within one year from the date of obtaining the license;

b) where it is confirmed that the license is obtained by fraudulent means;

c) where the broadcasting station suspends its transmission for more than one month without good cause;

d) where a court orders the closure of the station;

e) where the licensee, by its own initiative, stops the service;

f) where the provisions of Article 30(4) of this Proclamation are violated;

g) where the licensee fails to discharge its obligations under Article 27 of this Proclamation.

፪/ በባለሥልጣኑ ውሣኔ ቅር የተሰኘ የብሮድ ካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ውሣኔው በደረሰው በ፲፬ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል። ቦርዱም አቤቱታ በቀረበለት በ፴ ቀናት ውስጥ ውሣኔ መስጠት አለበት።

፫/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሀ) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ሥርጭቱን ለመጀመር ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ያጋጠመው መሆኑ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ካገኘ ሥርጭቱን ለመጀመር የሚያስችል ከስድስት ወር የማይበልጥ ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቀድለት ይችላል።

## ክፍል አራት
## በብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች ስለሚሠራጩ ፕሮግራሞች

### ፴. ጠቅላላ

፩/ ማንኛውም ለሥርጭት የሚቀርብ ፕሮግራም የተለያዩ አመለካከቶችን በማንጸባረቅ ሕብረተሰቡን በአጠቃላይ እንዲያገለግል ሚዛናዊ ሆኖ መቅረብ አለበት።

፪/ ማንኛውም ለሥርጭት የሚቀርብ ፕሮግራም ይዘቱና ምንጩ ትክክለኛ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

፫/ ማንኛውም ዜና ከአድልዎ የጸዳ፣ ትክክለኛና ሚዛናዊ መሆን አለበት።

፬/ ማንኛውም ለሥርጭት የሚቀርብ ፕሮግራም

ሀ) የሰው ልጆችን ሰብዕናና ነፃነት ወይም ሥነ ምግባርን የሚፃረር ወይም የሌሎችን እምነት የሚያንኳስስ፣

ለ) በመንግሥት ፀጥታ ወይም በሕገ መንግሥቱ መሠረት በተቋቋመው የመንግሥት አስተዳደር ወይም በአገር መከላከያ ኃይል ላይ የወንጀል ድርጊት የሚፈጽም፣

ሐ) የግለሰብን፣ የብሔር ብሔረሰብን፣ የሕዝብን ወይም የድርጅትን ስም የሚያጠፋ ወይም በሐሰት የሚወነጅል፣

መ) ብሔረሰብን ከብሔረሰብ የሚያጋጭ ወይም በሕዝቦች መካከል የእርስ በርስ ግጭት የሚያነሳሳ፣ ወይም

ሠ) ጦርነት የሚቀሰቅስ፣

መሆን የለበትም።

2/ Where a broadcasting service licensee is aggrieved by the decision of the Authority, it may submit its grievance to the Board within 14 days from the date of receipt of the decision. The Board shall give its decision within 30 days from submission of the grievance.

3/ Where the Authority confirms the existence of force majeure which hindered a broadcasting service licensee from commencing transmission within the period referred to in sub-article 1(a) of this Article, It may allow additional time, not exceeding six months, for commencement of the transmission.

## PART FOUR
## TRANSMISSIONS OF PROGRAMS BY BROADCASTING SERVICE LICENSEES

### 30. General

1/ Any program to be transmitted shall reflect different and balanced viewpoints to serve the public at large.

2/ The accuracy of the content and source of any program to be transmitted shall be ascertained.

3/ Every news shall be impartial, accurate and balanced.

4/ Any program intended for transmission may not:

a) violate the dignity and personal liberty of mankind or the rules of good behavior or undermine the belief of others;

b) commit a criminal offense against the security of the State, the constitutionally established government administration or the defense force of the country;

c) maliciously accuse or defame individuals, nation/nationalities, peoples or organizations;

d) cause dissension among nationalities or instigate dissension among peoples; or

e) incite war.

## ፴፩. የልጆችን ደህንነት ስለመጠበቅ

፩/ የልጆችን አመለካከት፣ ስሜትና አስተሳሰብ ሊጎዱ የሚችሉና ወደአልተፈለገ አቅጣጫ እንዲያዘነብሉ የሚገፋፉ የሬዲዮና የቴሌቭዥን ሥርጭቶችን ልጆች ሊመለከቱና ሊያዳምጡ በሚችሉበት ሰዓት ማስተላለፍ የተከለከለ ነው::

፪/ ከምሽቱ ፭ ሰዓት እስከ ንጋቱ አስራ አንድ ሰዓት ድረስ ልጆች የሬዲዮና የቴሌቭዥን ስርጭቶችን ሊያዳምጡና ሊመለከቱ አይችሉም ብሎ መገመት ይቻላል::

## ፴፪. ስለአገራዊ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ የሥርጭት ፕሮግራም

፩/ ማንኛውም አገር አቀፍ ስርጭት ከሳምንታዊ ስርጭት ጊዜው ቢያንስ ፷ በመቶ ለአገራዊ ፕሮግራሞች ማዋል አለበት::

፪/ ማንኛውም ክልላዊ ስርጭት ከሳምንታዊ የስርጭት ጊዜው ቢያንስ ፷ በመቶው ክልሉን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች ማዋል አለበት::

፫/ ማንኛውም አካባቢያዊ ስርጭት ከሳምንታዊ የስርጭት ጊዜው ቢያንስ ፷ በመቶው አካባቢውን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች ማዋል አለበት::

## ፴፫. ማስታወቂያ

፩/ ማስታወቂያ ከሌሎች ፕሮግራሞች የተለየ መሆኑ በግልጽ እንዲታወቅ ሆኖ መተላለፍ አለበት:: በሌሎች ፕሮግራሞች ይዘት ላይ ተጽዕኖ ማድረግም የለበትም::

፪/ የንግድ ማስታወቂያ እውነተኛ፣ የማያሳስትና ሕጋዊ የንግድ እንቅስቃሴን የሚያመለክት መሆን አለበት::

፫/ የሌላውን ምርት ወይም አገልግሎት በማጥላላት ወይም በማንኳሰስ ማስታወቂያ ማስተላለፍ የተከለከለ ነው::

፬/ የሥርጭት ጊዜው ከ፳ ደቂቃ በማይበልጥ በማናቸውም ፕሮግራም ወይም በሕፃናት ፕሮግራም ጣልቃ ማስታወቂያ ማስተላለፍ የተከለከለ ነው::

## ፴፬. የተከለከሉ ማስታወቂያዎች

የሚከተሉት ማስታወቂያዎች በማናቸውም የብሮድካስት አገልግሎት እንዳይተላለፉ ተከልክሏል፤

## 31. Protecting the Well-being of Children

1/ radio or television transmission programs that may corrupt the outlook of children or harm their feelings and thinking or encourage them to undesirable behavior shall not be transmitted at hours during which children normally watch or listen to such programs.

2/ Children are presumed not to listen or watch to radio or television transmissions from 11:00 o'clock in the evenings up to 5:00 o'clock in the morning.

## 32. National, Regional and Local Transmission Programs

1/ Any national transmission program shall allocate at least 60% of its weekly transmissions to national programs.

2/ Any regional transmission program shall allocate at least 60% of its weekly transmissions to programs that relate to regional affairs.

3/ Any local transmission program shall allocate at least 60% of its weekly transmissions to programs that relate to the local affairs.

## 33. Advertisements

1/ Any advertisement shall be transmitted in a manner that clearly differentiates it from other programs. It shall not also affect the contents of other programs.

2/ Commercial advertisement shall be truthful, not misleading and publicize lawful trade activities.

3/ The transmission of malicious or undermining advertisement on the products or services of others shall be prohibited.

4/ Broadcasting advertisement by interrupting any program the transmission time of which is not more than 20 minutes or children's program shall be prohibited.

## 34. Prohibited Advertisements

Broadcasting the following advertisements shall be prohibited:

፩/ የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን፣ የሴቶች ሰብአዊ መብትና ክብርን የሚያንኳስሱና የሚጋፉ ማናቸውም ማስታወቂያዎች

፪/ የሲጋራና ሲጋራ ነክ ማስታወቂያዎች፤

፫/ የአደንዛዥነት ባህርይ ያላቸው ዕጾችን የሚመለከቱ ማስታወቂያዎች፤

፬/የአልኮል መጠናቸው ከ፲፪ በመቶ በላይ የሆኑ መጠጦችን የሚመለከቱ ማስታወቂያዎች፤

፭/ ማናቸውም ያለ ሐኪም ትዕዛዝ ሊሰጡ የማይችሉ መድኃኒቶችን በቀጥታ ተጠቃሚ እንዲገዛ የሚገፋፉ ማስታወቂያዎች፤

፮/ ሌሎች በሕግ የሚከለከሉ ማስታወቂያዎች::

1/ Any advertisement that violetes gender equality and that disregards the dignity and human rights of women

2/ cigarette and cigarette related advertisements;

3/ advertisements related to narcotic drugs;

4/ advertisements of liquors with more than 12% alcoholic contents;

5/ advertisements that encourage users to buy medicine that cannot be administered without medical prescription;

6/ other advertisements prohibited by law.

## ፴፭. ለማስታወቂያ የሚመደብ ጊዜ

የማስታወቂያ ጣቢያ ካልሆነ በቀር በማናቸውም የሥርጭት ጣቢያ ለማስታወቂያ የሚመደበው ጊዜ ከየዕለቱ ወይም ከአንድ ከተለየ ኘሮግራም የሥርጭት ጊዜ ውስጥ ከ፳ በመቶ መብለጥ የለበትም::

## 35. Allocation of Advertisement Period

Unless it is an advertisement broadcasting station, any broadcasting station shall not allocate more than 20% of its daily transmission or in a particular programme time for advertisements.

## ፴፮. በስፖንሰር ስለሚቀርብ ኘሮግራም

፩/ በስፖንሰር የሚቀርብ ፕሮግራም ይዘትና የጊዜ ሠሌዳ በስፖንሰሩ ተፅዕኖ ሥር መውደቅ የለበትም:: በተለይም በፕሮግራሙ ይዘት ዉስጥ የስፖንሰሩ ምርት ወይም አገልግሎት እንዲሸጥ ወይም እንዲከራይ መቀስቀስ የለበትም::

፪/ ማስታወቂያ እንዳይነገርላቸው በሕግ የተከለከሉ ምርቶችን የሚያመርቱ ወይም የሚሸጡ ወይም አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ ሰዎች ስፖንሰር ሊሆኑ አይችሉም::

፫/ በስፖንሰሩና በጣቢያው መካከል ስምምነት ካልተደረገ በቀር ስፖንሰር በተደረጉ ፕሮግራሞች ጣልቃ ሌሎች የንግድ ማስታወቂያዎች እንዲገቡ አይፈቀድም::

፬/ በስፖንሰር በሚቀርብ ፕሮግራም የስፖንሰር አድራጊው ስም ቢያንስ በፕሮግራሙ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ መገለጽ አለበት::

## 36. Sponsored Program

1/ The content and timetable of a sponsored program shall not fall under the influence of the sponsor. In particular, a sponsored program shall not agitate the sale or hire of the sponsor's products or services.

2/ Persons who produce or sell goods or render services whose advertisement is prohibited by law shall not be sponsors.

3/ Unless otherwise agreed between the sponsor and the station, other commercial advertisements may not be transmitted by interrupting sponsored programs.

4/ The name of the sponsor shall be announced at least at the beginning and end of every sponsored program.

## ክፍል አምስት
## የባለፈቃድ ግዴታዎች

### ፴፯. ተጠሪን ስለማሳወቅ

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ለሚያሰራጨው ፕሮግራም ኃላፊ አድርጎ የሚመደበውን ሰው ለባለሥልጣኑ ማስታወቅ አለበት። በኃላፊነት የተመደቡት ሰዎች ከአንድ በላይ ከሆኑ የእያንዳንዱ ሰው የኃላፊነት ድርሻ በግልጽ ተለይቶ መታወቅ አለበት።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ የባለፈቃዱን ኃላፊነት አያስቀረውም።

### ፴፰. ፕሮግራም ቀርጾ ስለመያዝ

፩/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ዜናን ጨምሮ ያሰራጨውን ፕሮግራም ለ፴ ቀናት ቀርጾ ማስቀመጥ አለበት። በፕሮግራሙ ውስጥ ቀደም ሲል የተቀረጸ ፕሮግራም ወይም ፊልም ተካትቶ ከሆነ አብሮ መቀመጥና በተፈለገ ጊዜ ሊገኝ መቻሉ መረጋገጥ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለቁ በፊት በተላለፈው ፕሮግራም ላይ ቅሬታ ከቀረበ ቅሬታው አግባብ ባለው ሕግ ውሣኔ እስከሚያገኝ ድረስ ሪኮርዱ ተይዞ ይቆያል።

፫/ ለቁጥጥር ወይም የቀረበ ቅሬታን ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለፈቃዱ የያዘውን ፕሮግራም ቅጅ በራሱ ወጭ ለባለሥልጣኑ ወይም በሕግ መሠረት ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል የማቅረብ ግዴታ አለበት።

### ፴፱. መረጃ ስለመስጠት

ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በእያንዳንዱ ሥርጭት መጀመሪያና መጨረሻ ላይ የሥርጭት ጣቢያውን ስም መግለጽ አለበት። የፕሮግራሙ አዘጋጅም በፕሮግራሙ መጀመሪያ ወይም መጨረሻ በስም መጠቀስ አለበት።

### ፵. ቁጥጥር እንዲደረግ ስለመፍቀድ

ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የማሠራጫ ጣቢያውን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፬ መሠረት ለሚደረግ ቁጥጥር ክፍት የማድረግና የሚጠየቁ ሰነዶችንም የማቅረብ ግዴታ አለበት።

## PART FIVE
## OBLIGATIONS OF LICENSEES

### 37. Notification of Responsible Person

1/ A broadcasting service licensee shall notify the Authority the person who has been assigned to be responsible for the transmission of programs. Where several persons have been assigned for such position, the responsibility of each of them shall be clearly defined.

2/ The provisions of sub-article (1) of this Article shall not relieve the licensee of its responsibilities.

### 38. Keeping of Program Records

1/ A broadcasting service licensee shall keep the record of every transmitted program, including news, for 30 days. Where the program contains a previously recorded program or film, such program or film shall be included in the rerecord in such a way that it is accessible when required.

2/ Where a complaint is forwarded against a program before the expiry of the time limit specified in sub-article (1) of this Article, the record shall be kept until the case is decided in accordance with the appropriate law.

3/ Where a program is needed for inspection or to investigate a complaint lodged against it, the licensee shall, at its own expense, provide a copy of the program to the Authority or to the organ authorized by law to adjudicate the case.

### 39. Providing Information

Any broadcasting service licensee shall announce the name of the station at the beginning and end of every transmission. The producer of the program shall also be mentioned by name at the beginning or end of the program.

### 40. Allowing Access for Inspection

Any broadcasting service licensee shall have the duty to give access to its broadcasting station and to furnish the required documents for inspection to be conducted pursuant to Article 44 of this Proclamation.

## ፵፩. አስቸኳይ መንግሥታዊ መግለጫዎችን ስለማስተላለፍ

፩/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ በመከሰቱ፣ የተፈጥሮ አደጋ በማጋጠሙ ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ በመከሰቱ ምክንያት የፌዴራል መንግሥት ወይም ማንኛውም ክልል የሚሰጣቸውን አስቸኳይ መግለጫዎች ያለክፍያ ማስተላለፍ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች መንግሥታዊ ማስታወቂያዎች በሚተላለፉበት ጊዜ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ ክፍያ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ይሆናል፡፡

## ፵፪. መልስ የመስጠት መብትን ስለማስከበር

፩/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ባስተላለፈው ፕሮግራም መብቱ ተነክቷል ወይም በአግባቡ አልቀረበም ለሚል ሰው ስለጉዳዩ መልስ ለመስጠት ያለውን መብት ማክበር አለበት፡፡

፪/ ባለፈቃዱ መልስ ሰጭው የሚሰጠውን መልስ በተመጣጣኝና በተመሣሣይ ጊዜ በግልጽ የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፡፡

## ፵፫. የምርጫ ጊዜ መግለጫዎችን ስለማሠራጨት

፩/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችና የምርጫ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በምርጫ ወቅት ዓላማቸውንና ፕሮግራሞቻቸውን ለሕዝብ እንዲያስተዋውቁ ወይም መግለጫ እንዲያስተላልፉ ነፃ የአየር ጊዜ መመደብ አለበት፡፡ አፈጻጸሙ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም ዕጩ ተወዳዳሪ የምርጫ ውድድር ማስታወቂያ ማስተላለፍ ይችላል፡፡

፫/ ለምርጫ ውድድር ማስታወቂያ የሚጠየቀው ክፍያ ለንግድ ማስታወቂያ ከሚጠየቀው ክፍያ ሊበልጥ አይችልም፡፡

፬/ የሥርጭት ጊዜ የተሰጠው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ዕጩ ተወዳዳሪ ለተሠራጨው ፕሮግራም ወይም መግለጫ ሕጋዊነት ኃላፊ ይሆናል፡፡

## 41. Transmission of Emergency Government Statements

1/ Any broadcasting service licensee shal transmit, free of charge, emergency statements given by the federal or a regional state government due to the occurrence of an incident that endangers the constitutional order of the country, a natural disaster or an epidemic that threatens public health.

2/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article, the right of the broadcasting service licensee to demand payment when transmitting other governmental statements shall be respected.

## 42. Duty to Respect the Right to Reply

1/ Any broadcasting service licensee sha respect the right of a person to give reply concerning an issue when he alleges that a transmitted program has encroached on his right or failed to be presented properly.

2/ The broadcasting service licensee sha clearly transmit the reply at a proportional and similar time.

## 43. Transmission of Election Period Statements

1/ Any broadcasting service licensee sha allocate free airtime for political organization and candidates registered in accordance wit the relevant law, to publicize their objective and programs to the people or to transm statements during election period. Th implementation of this provision shall b determined by directives to be issued by th Authority.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of th Article, any political organization ( candidate may transmit electio campaign advertisement.

3/ The fee to be charged for electic campaign advertisement may not excee the fee charged for commerci advertisements.

4/ The political organization or candida provided with air time shall b responsible for the legality of the progra or statement transmitted.

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፵፬. ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን

፩/ ባለሥልጣኑ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና በዚህ አዋጅ መሠረት የሰጣቸው ውሣኔዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ኢንስፔክተሮችን ለመመደብ ይችላል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተመደበ ኢንስፔክተር የብሮድካስት አገልግሎት በሚያካሂድ ድርጅት ውስጥ በሥራ ሰዓት ለመግባትና ቁጥጥር ለማድረግ ይችላል::

፫/ ኢንስፔክተሩ ቁጥጥር ሲያደርግ ማንኛውንም የብሮድካስት መሣሪያ ለመመርመር፣ አግባብ ያላቸውን ሰነዶች ለማየትና ቅጅው እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይችላል::

፬/ ኢንስፔክተሩ ቁጥጥር ወደሚያደርግበት ሥፍራ ለመግባት የመታወቂያ ወረቀቱን ማሳየት አለበት::

### ፵፭. ቅጣት

በወንጀል ሕግ የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣

፩/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፲፰ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ሰው ከብር ፶ሺ በማያንስና ከብር ፻ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

፪/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፴ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) ወይም (፫) በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ባለፈቃድ ከብር ፲ሺ በማያንስና ከብር ፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

፫/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፴፩ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ባለፈቃድ ከብር ፲ሺ በማያንስና ከብር ፳፭ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

፬/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፴፫(፫) ወይም አንቀጽ ፴፬ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ባለፈቃድ ከብር ፳ሺ በማያንስና ከብር ፴ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

፭/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፴፫ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) ወይም (፬)፣ አንቀጽ ፴፭ ወይም ፴፮ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ባለፈቃድ ለመጀመሪያ ጊዜ ከባለሥልጣኑ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤ ድጋሚ ጥፋት ከፈጸመ ከብር ፭ሺ በማያንስና ከብር ፲ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

## PART SIX
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 44. Power of Inspection

1/ The Authority may assign inspectors to ensure the compliance of provisions of this Proclamation and its decisions rendered in accordance with this Proclamation.

2/ An inspector assigned in accordance with sub-article (1) of this Article shall have the power to enter and inspect a broadcasting service organization during working hours.

3/ The inspector may, in the course of his inspection, examine any broadcasting instruments, refer to relevant documents and demand a copy thereof.

4/ When the inspector enters into the inspection site, he shall show his identity paper.

### 45. Penalty

Unless punishable with more severe penalty under the Criminal Code, any person found guilty of violating:

1/ Article 18 of this Proclamation shall be punishable with a fine not less than Birr50,000 and not exceeding Birr100,000;

2/ Sub-Article (1), (2) or (3) of Article 30 of this Proclamation shall be punishable with a fine not less than Birr10,000 and not exceeding Birr50,000;

3/ Article 31 of this Proclamation shall be punishable with a fine not less than Birr10,000 and not exceeding Birr25,000;

4/ Article 33(3) or 34 of this Proclamation shall be punishable with a fine not less than Birr20,000 and not exceeding Birr30,000;

5/ Sb-Aticle (1), (2) or (4) of Article 33, Article 35 or 36 of this Proclamation shall be given a warning in writing for the first violation, and be punishable with a fine not less than Birr5,000 and not exceeding Birr10,000 for the second violation;

፮/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፴፯ ወይም ፴፱ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ባለፈቃድ ለመጀመሪያ ጊዜ ከባለሥልጣኑ የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤ ድጋሚ ጥፋት ከፈጸመ ከብር ፭ሺ. በማያንስና ከብር ፲፭, በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

፯/ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፴፱ ወይም ፵፫ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ባለፈቃድ ከብር ፳ሺ. በማያንስና ከብር ፶ሺ. በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል::

## ፵፮. ስለውርስ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴(፬) የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው ከዋናው ቅጣት በተጨማሪ ለብሮድካስት አገልግሎት ያዋለው ንብረቱ ይወረሳል::

## ፵፯. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ይህን አዋጅ በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ መመሪያዎችን ሚኒስቴሩ ማውጣት ይችላሉ::

## ፵፰. የተሻረ ሕግ

የብሮድካስት አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፰/፲፱፻፺፩ በዚህ አዋጅ ተሽሯል::

## ፵፱. የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት

፩/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አግባብነት ያላቸው የሀገሪቱ የፕሬስ አዋጅ ድንጋጌዎች አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች በብሮድካስት አገልግሎት ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ::

፪/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም::

## ፶. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

6/ Article 37 or 39 of this Proclamation shall be given a warning in writing for the first violation, and be punishable with a fine not less than Birr5,000 and not exceeding Birr15,000 for the second violation;

7/ Article 39 or 43 of this Proclamation shall be punishable with a fine not less than Birr20,000 and not exceeding Birr50,000.

## 46. Confiscation

The property of a person used for broadcasting shall, in addition to the principal penalty, be confiscated if that person is found, in accordance with the provisions of the relevant criminal law, guilty of violating the provision of Article 30(4) of this Proclamation.

## 47. Power to issue Regulations and Directives

The Council of Ministers and the Ministry may, respectively, issue regulations and directives necessary for the proper implementation of this Proclamation.

## 48. Repeal

The Broadcasting Proclamation No. 178/1999 is hereby repealed.

## 49. Applicability of Other Laws

1/ Without prejudice to the provisions of this Proclamation, the relevant provisions of the Press Proclamation No. 34/1992, with the exception of Article 7 and 13 thereof, shall be applicable to broadcasting services.

2/ No law shall, in so far as it is inconsistent with the provisions of this Proclamation, be applicable to matters provided for by this Proclamation.

## 50. Effective date

This Proclamation shall come in to force up or Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 23 day of July, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERA**
**DEMOCRATICREPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት